# መድሐኒአለም ይፋረደኝ ! – ነቢዩ ሲራክ

**April 23, 2015** - ግጥም




ማጣቱ ዘልቆ ሳይጎዳኝ ፣
ድህነቱን ችየ በኖርኩኝ ፣
እህ ብየ ተመስገን ብየ ኑሮ በገፋሁኝ ፣
የመኖሬን ተስፋ ቀማችሁኝ ፣
ልጀን ወዳጀን ነጠቃችሁኝ ፣
ደጋፊየ ጠዋሪየን በግፍ ቀማችሁኝ **!**
እኔማ **....** ደካማ እናት ነኝ ፣
ልጀን በጨካኞች በግፍ ያጣሁኝ ፣
አሳቢ ልጀን የተቀማሁ ፣ የጎደለብኝ ፣
እኔማ አድሜ ጠገብ ፣ ደከማ ነኝ ፣
ለበቀል የሚሆን ጉልበት የከዳኝ ፣
የተገፊ እናት ነኝ ፣ ሀዘን ጠልቆ የተሰማኝ ፣
አዎ**!** አቅም ያጣሁ ምንዱብ እናት ነኝ **!**
ብቻ ተስፋየ በሱ ነው ፣ በማይተወኝ ፣
የፈጠረኝ መድሐኒአለም ይፋረደኝ ፣
በቀል አይቀርም ተስፋ አለኝ **!**
እሱ አንድየ ይድረስልኝ **!**
መድሐኒአለም ይፋረደኝ **! ”**
አዎ እናታለም ፣ መድሐኒአለም ይፋረደን **!!!**
አዎ እናት አለም **...**
የበቀል አምላክ ዝም አይልም ፣
መድሐኒአለም ይፈርዳልም **!**ነቢዩ ሲራክ
በጨለመው ሚያዝያ **15** ቀን **2007** ዓም